የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.51
ADDIS ABABA 25th May, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ…….ገጽ ፲፪ሺ፭፻፶፭

**Content**

Proclamation No.1200/2020

Export-Import Bank of Korea Loan Agreement for financing the Establishment of Addis Ababa Bus Rapid Transit Project Ratification Proclamation ……………………………......................Page 12,555

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻/፪ሺ፲፪**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ስልሳ ሶስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (፷፫ ሚሊዮን ዩ.ኤስ.ዲ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል መጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION NO. 1200/2020**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF KOREA**

WHEREAS, the Loan Agreement, between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea stipulating that Export-Import Bank of Korea provide to the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of Sixty Three Million United States Dollar (63,000,000 USD) for financing the Establishment of Addis Ababa Bus Rapid Transit Project, was signed in Addis Ababa on 1st day of April, 2020;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 5th day of May, 2020;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል መጋቢት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር ETH-7 ፀድቋል፡፡

## ፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ስልሳ ሶስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር (፷፫ ሚሊዮን ዩ.ኤስ.ዶ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the “Export-Import Bank of Korea Loan Agreement for financing the Establishment of Addis Ababa Bus Rapid Transit Project Ratification Proclamation No. 1200/2020”.

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement Number ETH-7 signed in Addis Ababa on 1st day of April, 2020 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of Sixty Three Million United States Dollar (63,000,000 USD) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 25th day of May, 2020**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**